# “የግሉ ፕሬስ” ነፃ ፕሬስ ይሁን

ሲቲና (ከሐረር)

ሐሣብን የመግለፅና የመቀበል መብት ከሰው የፊተጥራዊ ባሕሪ የመነጨ እንጂ በሌላ ውጫዊ ወገን የተሰጠ ወይም የሚሰጥ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የዚህ ሰብአዊ መብትና ነፃነት ለመጀመሪያ ጊዜ እውቅና ያገኘው ለዚህ መብትና ነፃነት መሠረታዊ እውቅና በሰጠው የሽግግር መንግስቱ እንደ ሕገ መንግስት ይገለግለበት በነበረበው ቻርተር መሠረት በ1984 ዓ.ም በወጣው የፕሬስ ሕግ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ በርካታ የግል መፅሔቶችና ጋዜጦች እንደ አሸን እየታተሙ መሠራጨት ጀመሩ፡፡

ከዚያ ቀደም በነበሩት ሁለት የመንግስት ሥርአቶች ኢትዮጵያውያን እንደማንኛውም ሰው በነፃ የማሰብ፣ ያመኑበትን የመናገርና የመፃፍ እንዲሁም የመረጡትን የማድመጥ መብት ሳይቀር በሌላ ሶስተኛ አካል ይወሰንላቸው ነበር፡፡ በወታደራዊው የደርግ ሥርዓት በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ከሚሠራጩ አመለካከቶችና መረጃዎች ውጭ በአየር ላይ የተበተኑ የውጭ የሬዲዮ ሞገዶችን እንኳን እቤታችን ቁጭ ብለን ማድመጥ እንደ ከዳተኛ ስለሚያስቆጥር ከድርጊቱ እንቆጠብ ነበር፡፡

እንግዲህ ይህን አምባገነን የወታደራዊ ቡድን - አዛዥ ናዛዥ፣ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት የተካው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ከዚያም የኢፌዴሪ መንግስት ነው፡፡ ሐሣብን ለመግለፅና ለመቀበል መብት ሕገ መንግስታዊ ዕውቅና የሰጠውም ይኸው መንግስት ነው፡፡

ህዝቡ የሥልጣን ባለቤትነቱን የሚያረጋግጠው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ድምፅን በሰጠው ተወካዩ ሲተዳደርና ሐሣብን በነፃነት መግለፅና መቀበል ሲችል ብቻ ነው፡፡ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት በመሆኑ፣ ይህን ሥልጣን ለየትኛው ወገን በውክልና መስጠት እንዳለበት ለማወቅ መረጃ በነፃነት ማግኘት ደግሞ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ህብረተሰቡ ይወክለኛል ያለውን ወገን “በዚህ መልክ መተዳደር እፈልጋለሁ” ብሎ በቀረፀው ሕገ መንግስት እና ሌሎች ከዚሁ የመነጩ ሕጎች፣ ደንቦችና ፖሊሲዎች መሠረት እያስተዳደረው መሆኑን ማወቅ የሚችለው፣ ሐሣብን በነፃነት የመግለጽንና የመቀበል መብትና ነፃነት - የፕሬስ ነፃነት ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በተመሣሣይም መንግስትም

የውክልና ስልጣን የሰጠውን ሕዝብ ፍላጐት መረዳት የሚችለው ይሄው መብትና ነፃነት በተረጋገጠበት ሥርዓት ነው፡፡ የፕሬስ ነፃነት ዋነኛው የዴሞክራሲያዊ መንግስት - የሕዝባዊ መንግስት መገለጫ ነው፡፡ የዚህ መብትና ነፃነት ገደብ የሕዝብ መብትና ነፃነት ብቻ ነው፡፡

እንግዲህ በዚህ መሠረታዊ መርሕ ነው የኢፌዴሪ መንግሥት ሐሣብን የመግለፅ መብትና ነፃነትን፣ የፕሬስ ነፃነትን ያረጋገጠው፡፡ አሁን ያሉት በርካታ የግል ጋዜጠኞችና መፅሔቶች መሠራጨት የቻሉት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የህትመት ሚዲያውን ያህል ባይሆኑም አንድ ሦስት የግል የሬዲዮ /የኤፍ.ኤም/ ጣቢያ ሥርጭት ማድመጥ የቻልነው ለዚህ ሠብአዊ መብት ዕውቅና በሠጠው ሕገ መንግስት ነው፡፡

ይህ በጎ ሆኖ ሣለ፣ በተለይ የኢትየጵያ የግል ጋዜጠኞች ይህን መብት ያለ አግባብ የተጠቀሙበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ የተዛቡ መረጃዎችንና አመለካከቶችን በማሠራጨት ሕዝብ በአንድ ወገን ላይ መሠረተ ቢስ ጥላቻ /prejudice/ እንዲያድርበት፣ አንዱ የሕብረተሰብ ክፍል በሌላው ላይ እንዲነሳሳ፣ እርስ በርስ በጥርጣሬ እንዲተያዩ በማድረግ የመቻቻልን እሴት የሚያፋልሱ መረጃዎችና አመለካከቶች ሲሠራጩ ቆይተዋል፤ አሁንም እየተሰራጩ ነው፡፡ የፕሬስ ውጤት ባለቤቶቹ ያሻቸውን አመለካከትና አቋም መሠረት ያደረገ የኤዲቶሪያል ፖሊሲ የመቅረፅ መብት ቢኖራቸውም፤ እንደ ነፃ ፕሬስ የሕዝብን ዘላቂ ሠላም፣ ልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያረጋግጡ ሐቀኛና ሚዛናዊ መረጃና አመለካከቶችን ይዞ መውጣት ይጠበቅባቸዋል፣ «ነፃ ፕሬስ» የሚያሰኛቸውም ይሄው ነው፡፡

በአጠቃላይ «የኢትዮጵያ የግል ፕሬሶች፤ እንዲፈጠሩና እንዲንቀሣቀሱ ያስቻለውን ሕገ መንግስትና የመንግስት ሥርዓት ላይ አፍራሽ አካሄድን ተከትለዋል» ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ ነበር፤ በቅንነት ለታዘበው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ያመኑበትን አመለካከት የማንፀባረቅ መብት ቢኖራቸውም የሕዝብን መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች የመጋፋት መብትና ነፃነት የላቸውም፡፡ በሕገ መንግስቱና በፕሬስ ሕጉ ላይ የተቀመጡት መመሪያዎች የሁሉንም ዜጐች መብት በአግባቡ ሊያስተናግዱ በሚችሉ አኳኋን ነው፡፡ አንድ ሰው መብቱን የሚያስከብረው የሌላውን እየረገጠ መሆን የለበትም፡፡ መብትን የሚጠይቅ ሁሉ ግዴታውን ማወቅ ይጠበቅበታልና፡፡

ጋዜጠኝነት፣ እንደማንኛውም ሙያ ለሕዝብ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ቁሣዊና መንፈሣዊ ተጨማሪ እሴቶችን፣ ለመፍጠር የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እሴቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ ተቃራኒ የሆኑ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትሉ አመለካከትና አሉባልታዎችን የሚያሰራጩ ከሆነ፣ የፕሬስ ባለቤትና ጋዜጠኞች ገቢ - ትርፍና ደመወዝ ፍትሐዊ ካልሆነ የሙያ ሥነ ምግባር ከሚፈቅደው ውጪ ጥቅም እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ማለት "የበሬ ወለደን" ዜና በመዘገብ ህዝብንና መንግሥትን፣ ህዝብን እርስ በርሱ እንዲጋጭ በማድረግ ርካሽንና የዘቀጠን ተግባር በመፈፀም ዕለታዊ ጥቅምን ለማግኘት መሯሯጥ ይሆናል፡፡ ይህ ተራ ድርጊት ደግሞ መልካም ነገሮችን እንዳይመለከቱ ይጋርዳል፡፡ ኢ- ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ማንኛውም ጥቅማ ጥቅም ደግሞ ወንጀል ነውና በሕግ ያስጠይቃል፡፡

የፕሬስ ነፃነት በሕግ ከተረጋገጠበት 1984 ጀምሮ ባሉት አስራ ሰባት አመታት ያስተዋልናቸው የግል ጋዜጦች የተከተሉት አካሄድ በተደጋጋሚ የሕግን እና የሙያ ስነምግባርን ያላገናዘበ መሆኑን ማንም ነፃ ህሊና ያለው ዜጋ ሊፈርድ የሚችለው ሐቅ ነው፡፡ እንደ ጤዛ ለአፍታ ብልጭ ብለው የጠፉት፣ እንደ ቄጤማ ለወራት ታይተው የረገፉትን ማተሚያ ቤት ይቁጠራቸው፡፡ ያትሟቸው የነበሩትን አፍራሽ ሃሳቦች በዚህ ፅሑፍ መዳሰስ ስለማይቻል፣ እንዳመቺነቱ ለወደፊት ለማቅረብ ቃል እየገባሁ በዚህ ፅሑፍ መንደርደሪያ በሚሆን ጉዳይ ላይ መወሰንን መርጫለሁ፡፡

አገራችን ከ1983 ዓ.ም በፊት አንድም የጋዜጠኝነትን ሙያ የሚያስተምር ኮሌጅም ሆነ ዩኒቨርሲት አልነበራትም፡፡ በውጪ አገር ከተማሩ በጣት ከሚቆጠሩ ባለሙያዎች በስተቀር አብዛኛው ጋዜጠኛ የጋዜጠኝነትን ሙያ የተቀላቀለው በልምድና በፍላጐት ብቻ ነው፡፡ ይህ የሙያውን ሥነ ምግባር በቅጡ ያልተረዳው "ሙያተኛ ነኝ" ባይ መብትን መጠቀም እንጂ የሙያውን ግዴታዎች ለይቶ ያወቀ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ የተሳሳተ መረጃ ለሦስተኛ ሰው አሳልፎ መስጠት ምን ያህል አገርና ሕዝብን እንደሚጐዳ ጠንቅቆ የተረዳው አይመስልም፡፡

አገሪቱ ለነፃ ፕሬስ አዲስ በመሆኗ፣ እንደባህል ስላልዳበረ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የጋዜጠኝነት የሙያ ክህሎት ብቃት ያስከተላቸው ችግሮች መኖራቸው ሣይዘነጋ ከዚህ የተለየ ምክንያትም መኖሩን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች አሉ፡፡

ዘውዳዊውና ወታደራዊ አምባገነን ሥርአቶች ከተወገዱ ገና አጭር ጊዜ በመሆኑ የእነዚህ ሥርዓት አራማጅና የሥርዓቱ ተጠቃሚ የነበሩ ግለሰቦች እንዲሁም የስርዓቶቹ የፕሮፖጋንዳ ሠለባ የሆኑ አፈቀላጤዎቻቸው ከነአመለካከታቸው እስከአሁን ያሉ መሆናቸው ነው፡፡ ለማንኛውም ዜጋ የተረጋገጠው የፈቀዱትን አቋም መያዝና የፈለጉትን አመለካከት በሰላማዊ መንገድ የማራመድ ለሁሉም ዜጎች በእኩልነት የተሰጠ መብት ነው፡፡ የአሮጌዎቹ ሥርዓቶች አራማጆችና ናፋቂዎች እንኳን ያረጀ ያፈጀውን አመለካከታቸውን እንደፈለጉ የማንፀባረቅ እድል አግኝተዋል፡፡ መንግስትም ዜጎች የፈለጉትን አመለካከት በሰላማዊ መንገድ ማራመድ እስከቻሉ ድረስ ያለገደብ መብትን አጐናፅፏል፡፡ ሆኖም የድሮው ስርዓት አቀንቃኞች ግን ይህን መብት በአግባቡ የተጠቀሙበት አይመስሉም፡፡ መብትና ግዴታቸውንም ለይተው አልተረዱትም፡፡

የአሮጌው ሥርዓት አቀንቃኞች አምባገነናዊ በመሆናቸው ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን መቀበልና ማክበር አይችሉም፡፡ እነሱ እንደፈለጉ ሲያንቦጫርቁ የሌላውን መብት የነኩ አይመስላቸውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአምባገነኑ ወታደራዊው ደርግ ውድቀት ዋነኛ ድርሻ የነበረውን ኢሕአዴግን ሕያው ጠላት አድርገው ነው የሚመለከቱት፡፡ ለዚህም ነው የግሉ ፕሬስ እንደልቡ መፈንጨት ከጀመረበት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ እንደዚህ እንዲሆን የፈቀደለትን ሕገ መንግስት ሳይቀር በአደባባይ ሲያብጠለጥል የታየው፡፡ ያለፉት ሥርዓቶች ዋንኛ አቀንቃኝ የነበሩትና አሁን በተቃዋሚ ፓርቲ ስም የተደራጁት ኃይሎች ሥልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ በመሠረተ ቢስ ጥላቻ ላይ በመመስረት ርካሽ ተወዳጅነትን ለማግኘት ሲጥሩ ይታያሉ፡፡

ይሁንና ህብረተሰቡ ከባህሪያቸውና ከድርጊታቸው ማንነታቸውን የለየ በመሆኑ ያሰቡትን ማግኘት አልቻሉም፡፡ ይህ የቁም ቅዠታቸው እውን አለመሆኑን ሲረዱት ሕዝብን ለሁከትና ለብጥብጥ ለመቀስቀስ ሲሞክሩ ታይተዋል፡፡ ላም አለኝ... ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ደግሞ ሲጠቀሙበት የነበሩት በነፃው ፕሬስ ስም ያቋቋማቸውን የግል ፕሬሶች ናቸው፡፡ እነዚህ በነፃው ፕሬስ ስም የተቋቋሙት የግል ፕሬሶች ያለፈውን ሥርዓት ናፋቂ የሆኑትን ክፍሎች ለማርካት ሆን ተብሎ የተጀመሩ በመሆቸው ወደ ህብረተሰቡ ሰርፀው መግባት ባለመቻላቸው ከጅምሩ ከስመዋል፡፡

የኢትዮጵያ የግል ፕሬስ አብዛኞቹ እራሳቸውን “ተቃዋሚ ፕሬስ” ብለው ይጠሩ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡ ከላይ የገለጽነው ሃሳብ የግሉ ፕሬስ ያለበትን ቦታ በግልፅ ሊጠቁመን ይችላል፡፡ በመሠረቱ ተቃዋሚ ፓርቲ እንጂ “ተቃዋሚ ፕሬስ” የሚባል ነገር የለም፡፡ እርግጥ ፓርቲዎች የየራሳቸው ልሣን ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የፓርቲ ልሣን ግን ነፃ ፕሬስ አይደለም፡፡ እራሳቸውን “ተቃዋሚ ፕሬስ” ብለው ይጠሩ የነበሩት የግል ጋዜጦች ሚዛናዊነት በጐደለው ሁኔታ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ልሣን ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ የግል ጋዜጦችም እራሳቸውን “ተቃዋሚ ፕሬስ” ብለው መጥራታቸውን ከመተዋቸው በስተቀር አሁንም የሚታየው ቀድሞ ከተጠናወታቸው አባዜ ብዙዎቹ የተላቀቁ አይመስሉም፡፡ ሰላም !!